የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የፌደሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
of
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር ኬዳ/፹/ሬ.፩/5/3/4
No
ቀን 23/02/2011
Date

ለጫት እርሻ እርባታና ኢንዱስትሪ ውጤቶች አምራችና ላኪ አክስዮን ማህበር

ባሉበት

ጉዳዩ፡- የምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ

እርስዎ የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ማቅረብዎ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የፌዴሬሽን ምክር ቤት መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም በ5ኛ የፓርላማ ዘመን 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ላይ ከፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው አይደለም በማለት የሰጠውን የውሳኔ ግልባጭ 4/አራት/ ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ ሰጥተንዎታል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዶራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ከሰላምታ ጋር

ኬሪያ ኢብራሂም አሊ
የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ

ግልባጭ

- ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉደዳዮች አጣሪ ጉባኤ

አዲስ አበባ

- ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን

# 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

**መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም**

አመልካች፡- የጫት እርሻ እርባታና ኢንዱስትሪ ውጤቶች አምራችና ላኪ አክስዮን ማህበር

ተጠሪ፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ

**የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡**

**ውሳኔ**

አመልካች የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ. 101755 በቀን 22/3/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የንብረት ባለቤትነት ሕገ መንግስታዊ መብቴን የሚቃረን ስለሆነ የሕገ መንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

የጉዳዩም ፍሬ ሃሳብ የአሁን አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በድሬዳዋ ከተማ በቀድሞው ከፍተኛ 4 ቀበሌ 21 በአሁኑ ቀበሌ 7 ክልል ውስጥ በቀድሞው የቤት ቁ. 132 በኋላ የቤት ቁ. 1419 በአሁኑ አወቃቀር ደግሞ በኪራይ ቤቶች አስተዳደር የቤት ቁ. 1110 የሆነውን ሁለት ክፍል ቤት እና መጋዘን በካርታ ቁ. 2038 የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ የተሰጠኝን የክፍሉ ቀበሌ በህገ ወጥ መንገድ በ1974 ዓ.ም ቤቱን ተረክቦ 100 ብር እያከራየ ስለሆነ ቤቱን እንዲያስረክበኝና ቤቶቹ አለአግባብ በመወሰዳቸው የደረሰብኝን ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ቀርቦ በሰጠው መልስ አመልካች ቤቱ ከአዋጅ ቁ. 47/67 ድንጋጌ ውጪ የተወሰነለት መሆኑን ለሚመለከተው አካል አመልክተው ቤቱ እንዲመለስለት የተወሰነ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ይህን ጉዳይ ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቅርቦ ከማስወሰን ውጪ ለፍ/ቤት ሊያቀርብ አይገባም፤ ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም፤ ቤቶቹ በአዋጅ የተወረሱና ለረዥም ጊዜ በተከሳሽ እጅ የቆዩ የመንግስት ቤቶች ናቸው፤ ስልጣን ባለው አካል ከ1983 ዓ.ም በፊት ቤቶቹ ለአመልካች



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

እንዲመለስለት የተወሰነ ነገር የለም፤ አመልካች ያቀረበውም ካርታ ህጋዊ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች የአመልካች የግል ሀብት መሆናቸውንና በመንግስት ያልተወረሱ መሆኑን ያስረዳ ስለሆነ ተጠሪ ቤቶቹን ለአመልካች እንዲያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡ ተጠሪ በውሳኔው ላይ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢጠይቅም ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ባለመቀበል ይግባኙን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ አሁንም ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ በማቅረቡ ሰበር ሰሚ ችሎቱ አቤቱታውን ተቀብሎ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ ቤቶቹን ለአመልካች ሊያስረክብ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ለሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረቡት ቅሬታ ቤቶቹ የግል ሀብቶቼ ናቸው በመንግስትም አልተወረሱም የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድም ስላለኝ ውሳኔው የንብረት ባለቤትነት መብትን የሚቃረን በመሆኑ የሕገመንግስት ትርጉም ይሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ጉባኤውም የቀረበውን አቤቱታና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ እንደተመለከተው አመልካች ክርክር ያስነሳውን ቤት ሚያዝያ 5 ቀን 1974 ዓ.ም ከግለሰብ ሲገዙ በጊዜው አሰራር መሰረት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት /የአሁኑ ተጠሪ/ የቅድሚያ ግዥ መብቱን መጠቀም እንደማይፈልግ በደብዳቤ ቁጥር አ327/6035/74 በቀን 05/8/74 ዓ.ም የምስክር ወረቀት መስጠቱን፤ የድረዳዋ ማዘጋጃ ቤትም በቁጥር 2038 በቀን በ21/7/75 ዓ.ም የተፃፈ የከተማ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአመልካች መስጠቱንና በሌላ በኩል የድሬዳዋ ከተማ አጠቃላይ የከነማ ነዋሪዎች ማህበር ም/ቤት በቁ. 583 በቀን 24/07/1977 ዓ.ም የተፃፈ የስመ ሀብት ማዘዋወሪያ ሰነድ አመልካች ቤቱን ከአቶ እስማኤል ወራህ ገዝተው በህጉ መሰረት የፀደቀ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ የሰጣቸው መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ተጠሪ መ/ቤት ክርክር ያስነሳውን ቤት በቁጥጥሩ ስር በማድረግ ለተለያዩ ሰዎች ያከራይ እንደነበር ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ያመኑበት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱ በሕጋዊ መንገድ ተወርሶ በእጁ የሚገኝ ስለሆነ ለረዥም ጊዜ በእጁ መቆየቱ ደግሞ እንደተወረሰ የሕግ ግምት ይወስዳል የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡

አመልካችም ቤቱ እንዲመለስላቸው ለተለያዩ አካላት ሲያመለክቱ እንደነበር እና በተለይም የድሬዳዋ ከተማ አጠቃላይ ም/ቤት በቁ. አ4/394/2/81 በቀን 24/11/1981 ዓ.ም ቀበሌው ቤቶቹን ለአመልካች እንዲያስረክብ በመግለፅ ውሳኔ የሰጠበትን ሰነድ፤ የድሬዳዋ ራስ ገዝ አስተዳደር የከተማ ልማትና ቤቶች ኮንስትራክሽን መምሪያ ጽ/ቤት በቁጥር 2/10011/ከድሬጫለማ69/83 በቀን 10/12/83 ቤቱ ለአመልካች እንዲመለስ የወሰነውን ሰነድ፤ የድሬዳዋ ከተማ ከፍተኛ አራት የከነማ ወኪል በቀን 23/11/83 ዓ.ም ቤቱን አመልካች በሕጋዊ መንገድ ከግለሰብ ገዝቶ የባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ አቅርቧል፡፡ በተጨማሪም አመልካች ቤቱ እንዲመለስለት ለፕራይቬታይዘሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አቤቱታ አቅርቦ ኤጀንሲውም ቤቱ ከአዋጅ ውጪ በመመሪያ በቀላጤ ወይም በቃል ትዕዛዝ ስለመወሰዱ ወይም ከ1983 ዓ.ም በፊት በአዋጅ አስፈፃሚው አካል ቤቱ ለአመልካች እንዲመለስ ስለመወሰኑና ስለመፈቀዱ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ የኤጀንሲው ስልጣን አይደለም አይመዘገብም በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጓል፡፡

ከላይ የቀረቡት ሰነዶች የሚያስረዱት አመልካች ቤቱን አዋጅ ቁጥር 47/67 ከወጣ በኋላ በሕጋዊ መንገድ ከግለሰብ ገዝቶ ስመሀብቱንም ወደ ራሱ ካዛወረ በኋላ ተጠሪ ቤቱን በቁጥጥሩ ስር በማድረግ ለተለያዩ ግለሰቦች እያከራየ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ተጠሪ ቤቱ በሕጋዊ መንገድ ከአመልካች ለመወረሱ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ጉዳዩ የሚመለከተው አካልም በተለያዩ ጊዜያት ቤቱ ለአመልካች እንዲመለስ ሲወስንና ትዕዛዝ ሲሰጥ ቢቆይም ቤቱ ለአመልካች ሊመለስ አልቻለም፡፡ ተጠሪ የቤቱ ሽያጭ ሲደረግም የቅድሚያ ግዥ ፍላጎት ተጠይቆ ቤቱን መግዛት እንደማይፈልግ ገልፆ የምስክር ወረቀት ስለሰጠው አመልካች ቤቱን ገዝተው በሕጋዊ መንገድ የቤቱ ባለቤት መሆናቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለረዥም ጊዜ በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበሩ ቤቶች እንደተወረሱ ይቆጠራሉ በማለት ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተሰጠውን የሰበር ውሳኔ በመግለፅ ተጠሪ ቤቱን ሊለቅ አይገባም በማለት የሰጠውን ውሳኔ ስንመለከት አመልካች በተቃራኒው ቤቱ በመንግስት ያልተወረሰ ስለመሆኑ ባቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ያረጋገጡ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ስለመወረሱ ያስረዳው ነገር የለም፡፡ ስለዚህ ውሳኔው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 የተደነገገውን የአመልካችን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚቃረን ነው በማለት ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤቱ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ከዚህም በመነሳት ምክር ቤቱ ጉዳዩ በሕገመንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ታይቶ እንዲቀርብ መርቶት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይትና

ማጣራት ካደረገ በኋላ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚሰጥባቸው ጉዳዮች የኢፌዴሪ ሕገመንግስት ከጸደቀበት እና ስራ ላይ ከዋለበት 1987 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን የሚመለከት እንጂ ወደ ኋላ በመመለስ ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ ለ38 ዓመት በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበሩትን ንብረቶች ሁሉ የ1987ቱን ሕገመንግስት መሰረት በማድረግ ትርጉም ያስፈልጋቸዋል እየተባለ ወደ ግለሰቦች የሚመለስበት አግባብ ሊኖር አይገባም፡፡

ፍርድ ቤቶች በተያዘው ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሰጡት የኢፌድሪ ሕገ መንግስት ከፀደቀ በኋላ ነው ቢባል እንኳ አዋጅ ቁጥር 47/67ን ተከትሎ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ በቀላጤ ወይንም በግለሰቦች አላግባብ የተወረሱ ሰዎችን ጉዳይ አጣርቶ ውሳኔ የሚሰጥ አካል በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቋቁሞ ይሰራበት በነበረበት ወቅት የአሁን አቤቱታ አቅራቢዎች ጉዳያቸውን ማቅረብ ሲገባቸው ይህን ሳይጠቀሙ አሁን ጉዳዩን ማንሳት ለክርክር የሚቀርበውን ማስረጃ ታማኒነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥለው ይሆናል፡፡

በተለይም በጊዜ ርዝመት ምክንያት የማስረጃ መጥፋት እና የአያያዝ ጉድለትን ተጠቅመው የተጭበረበሩ ማስረጃዎችን በማቅረብ የመንግስት ንብረቶችን በግል ለመጠቀም የሚፈልጉ አካላትንም የሚያበረታታ ይሆናል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የምክር ቤታችን የሕገ መንግስትና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ቦታው ድረስ ሄዶ ባጣራበት ወቅት ለኮሚቴ የቀረበውን ማስረጃ ስንመለከት በ1974 ዓ.ም በወቅቱ በነበረው ስርዓት ጉዳዩ የሚመለከተው የቤቶች አስተዳደር ቤቶቹን በምን ምክንያት እንዲያስረክቡ ተጠየቀ የሚለው ባይገለጽም በውስጡ ያሉትን የግል ንብረታቸውን እንዲወስዱና ቤቶቹን ለመንግስት እንዲያስረክቡ የሚያዝ እንጂ ቤቱ የአመልካች እንደሆነ የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡

ስለሆነም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠውና ለረጅም ጊዜ በመንግስት እጅ ሆነው ጥያቄ ሳይቀርብባቸው የቆዩ ቤቶች የመንግስት እንደሆኑ ይቆጠራል በማለት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ስለሆነ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ምክር ቤቱ ወስኗል፡፡

## ትእዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ፡፡
2. የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያውቀው ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይላክ፡፡